# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 1-31/2023 የነበረው
## የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከኖቬምበር 1-30/2023 የሚኖረው
## የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2023
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....... 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 3

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 4

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 5

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 6

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ....... 7

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 8

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 8

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር ወር የበጋዉ ደረቅ፣ፀኃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በምስራቅ፣ሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛዉ አከባቢዎች ላይ የሚስተዋልበት ወቅት ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ማለትም የደቡብ፣ደቡብ ምሥራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ  የዝናብ ስርጭት የታየበት ሲሆን በኦክቶበር የሁለተኛዉ አስር ቀናት የተሻለ  የዝናብ ስርጭት የተስተዋለበት ነበር፡፡

በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ደግሞ የዝናቡ ስርጭት ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም አብዛኛዉን የሀገሪቱ ክፍሎች ያዳረሰ ነበር፡፡በተጨማሪም  በመካከለኛው፣ ሰሜን ምሥራቅና ሰሜን ምዕራብ ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ወቅቱን ያልጠበቀ የዝናብ ስርጭት ተስተውሎባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በኦክቶበር ወር ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአሶሳ 39.4፣35.4፣በቦሬ 37.5፣ በቻግኒ 32.4፣30.0፣በአርባ ምንጭ 106.7፣በጃራ 40.9፣81.2፣በአሊያ 31.8 እና 69.5፣በአማን 36.5፣ በቡሬ 32.2፣35.2፣32.6፣62.5፤ ቻግኒ 34.2፤ በዳንግላ 30.2፣በአቦቦ 60.0፣በጭራ 33.9፣በጋምቤላ 35.2፣በጋቲራ 35.7፣በጊኒር 75.5፣55.5፣47.0፣ በጂንካ 39.3፣38.0፣35.4፣በዶሎ ኦዶ 37.5፤ በሊሙገነት 52.2፣56.9፣72.6፣30.2፣ በማጂ 53.2፣  በሳዉላ 30.4፣41.8፣በባህር ዳር 38.4፣31.2፣በድሬ ዳዋ 39.2፣ በጎንደር 37.4፣40.8፣ በጎሬ 41.2፣በጅማ 34.3፣ በነቀምቴ 33.5፣በአይራ 42.5፣ በሀሮማያ  64.0፣ በአልጌ 50.0፣ በአንገር ጉቲን  43.0፣ በአይከል 65.7፣30.9 እና 33.3፣ በበደሌ 89.0፣33.0፤ በብላቴ 32.8፣ በቡርጂ 33.5፣ በደምቢ ዶሎ 33.5፣ በዶሎ መና 40.4፣ በኢጃጂ 80.0፣ በገለምሶ 32.2፣ በጊምቢ 53.2፣40.1፣64.1፣ በሀረር 41.8፣ በኮንሶ 36.2፣ በማጆቴ 53.8፣ በማሻ 70.2፣40.6፣ በመካነ ሰላም 42.5፣ በምዕራብ አባያ 31.0 እና 52፣ በኑራኤራ 33.9፣ በሳዉላ 47.5፣ በሻውራ 30.4፣31.5፣ በተርጫ 54.3፣ በወራቤ 55.9፣ በወላይታ ሶዶ 69.7፣33.4፣38.8፣30.0፣ እንዲሁም በያቤሎ 34.3፣36.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፈው በኦክቶበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ፋፋን፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ዋህግምራ፣ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣የኦሮምያ

ልዩ ዞን፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ሰሜን ሸዋ፣አዊ ዞን፤ከአፋር ክልል ዞን 3 እና 5፤ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣መተከል፣ከማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ማዠንግ፣ንዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ስልጤ፣ሀዲያ፣ከምባታ ጠምባሮ፣ዳዉሮ፣ወላይታ፣ጎፋ፣ሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና በአዲስ አበባ፣ ላይ ከ40-494 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ5-28 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፈው የኦክቶበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊና፣ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣አዊ ዞን፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ቄለም ወለጋ፣ቡኖ በደሌ፣ኢሉባቦር፣ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ቦረና፣ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ከማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣አኙአክ፣ማዠንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞኖች፣ሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤የደቡብ፤የማዕከላዊ እና የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ሀረሪ፣ድሬዳዋ እና በአዲስ አበባ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን የተመዘገበ ሲሆን፣የአፋር፣የትግራይ፣የምስራቅ እና ምዕራብ አማራ ዞኖች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡

በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በምስራቅ፣በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል (ምስል 2) ፡፡


ከ40 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል ፡-





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 1  ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2  ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነዉ የኦክቶበር ወር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፣ደቡብ ምሥራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በተለይም በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የነበረው እርጥበት በተሻለ መልኩ አብዛኛዉን የሀገሪቱ ክፍሎች ያዳረሰ ነበረ፡፡ ይህም የተገኘዉ እርጥበት በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ መሻሻል፣ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረዉ፡፡ እንዲሁም በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅና በሰሜን ምዕራብ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የሰብል ስብሰባ በሚከሄድባቸዉ አካባቢዎች ላይ አሉታዊ ጎን የነበረዉ ቢሆንም በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ውሃ አጠር ለሆኑ አካባቢዎች ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ የፈጠረ ነበር (ካርታ 4)




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር ወር  በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በደቡብ እና በምዕራባዊ የአገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት መጠን እንደነበራቸው የተተነተኑ ወራዊ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የላይኛው አዋሽ፣ ተከዜ፣ በታችኛው ዋቤ ሸበሌ፣  እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ባሮ አኮቦ  ተፋሰሶች  ላይ መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ሲሆኑ የተቀሩት በአብዛኛው አፍር ደናክል፣ ኦጋዴን ፣ አዋሽ እና ምስራቃዊ ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ከማመዘኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት የሚታይበት ሲሆን፤ ከዚህም ሌላ በተዳከመ ሁኔታ ቢሆንም እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ እየዘነበ ይቆያል፡፡

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት እንደሚኖራቸዉና ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥለዉ ወር ከኦሮሚያ ክልል አብዛኛዉ የወለጋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የባሌ፣ የቦረና የጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሱማሌ ክልል ዞኖች እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ የመካከለኛዉ ኢትዮጵያ ክልል፤ አርሲ፣ የምስራቅና የምዕራብ ሐረርጌ፣ ከአማራ ክልል ሁሉም የጎጃምና የጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 3፣ 5 እና 1፤ በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ያገኛሉ፡፡

# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ ኢጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው እርጥበት በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ይህም ሁኔታ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ መሻሻል፣ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበትና ለእንስሳት መኖና የውሃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ ሊኖር የሚችለው እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ሆኖም ግን በአንዳንድ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ኢጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ የሚኖረው ከባድ መጠን ያለው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተጨማሪም ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል የሚኖረው የተጠናከረ እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሰብሎች ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት፣ በተዳፋትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተት ሊያጋጥም ስለሚችል አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ከወዲሁ በግብርና ባለሙያዎች በመደገፍ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል፡፡

# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር የበጋ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ማለትም የባሮአኮቦ፣ ገናሌዳዋ፣ በመካከለኛውና በታችኛው ኦሞጊቤ፣ ዋቢሸበሌ፣ የታችኛው ስምጥሸለቆ እና ኦጋዴን፤ የተለያየየ መጠን ያለው እረጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በተፋሰሶቹ ውስጥ የሚገኙ ግድቦች እና የተለያዩ የውኃ አካላት የተሻለ የውኃ ክምችት እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡